የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)
Ethiopian People's Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

# ስማችን --- ኢወክንድ
# ልሳናችን---- ነቅንቅ

ግንቦት 5 ቀን 2002 ዓ.ም.

## ከወያኔ መጠንቀቅ በተኩላ እንዳንነጠቅ

የጥንት አያት ቅድመ አያቶቻችንን የነጻነት የተጋድሎ መንፈስ ቀለብ አድርገን፣ የቀደምት ወንድም እህቶቻችንን የትግል ፅናት ወርሰን የተነሳን ስለሆነን ነው በኢወክንድ ስም የተደራጀነው ።

ኋላ ቀርና አምባገነን የሆኑትን ሥርዓት ሲፋለሙ ለተሰው የቀደምት ወጣቶች ከበሬታ ስላለን ነው የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ብለን የተደራጀነው።

ላለፉት 40 ዓመታት በመስዋእትነት የታጀበ የቆራጥነት ምጥ አምጦ የወለደን የአንድ ዓመት ለጋ ድርጅት ብንሆንም፣ እሳትን ከውሃ ፤ ምርትን ፤ ከግርዱ አርበኛን ከባንዳ ፤ ፀረ ኢትዮጵያዊውን ከኢትዮጵያዊው ፤ የመለየትን ፀጋ በነ ፀጋዬ ፍዳ ፀጋ ተላባሰናልና ኩራት ኩራት ይለናል ።

ታዲያ እኛ ሳንፈጠር ሕዝባዊ ገድል የፈፀሙትን ስናስታውስ ዛሬ የጊዜው አረሙቻዎች ያደረሱትን ፀረ ወጣት ፍጅት ይረሳሉ ተብለን እንደ ጌኛ መቀጠራችን ኩፉኛ ያበግነናል፤ ጭራሽ ያጠብቀናል። የኢትዮጵያ ጠላት የሆነውን ወያኔን ለማጥፋት በብዛት ያሰባስበናል።

ይህ የመርገምት ጎተራው ሞልቶ የፈሰሰ ተባይ ሥርዓት ባለፉት 19 ዓምት የቀለቡ ማወራረጃ ያደረገው የኢትዮጵያ ወጣቶችን ደም መሆኑን ማን ይዘነጋለታል? የራሱ የገዳዩ ፍጡሮች ገፋ ሲልም ህሊናቸውን የጥቅም ሞራ የሸፈነባቸው ካልሆኑ በቀር።

- እኛ ውጣቶች በሀገራችን ተወለድንባት እንጂ መቼ ተማርንባት ? ያልተመረመረ ፀረ ኢትዮጵያ የትምህርት ፖሊሲ ፈጀን እንጂ?
- ቁቤ ፤ላቲን ወጋጎዳ ወዘተርፈ..... እያለ ወያኔ አደነቆረን እንጂ
- እኛን ወጣቶችንን ቤተ ሠቦቻችንን በዘር ምንጫቸውና በፓለቲካ አመለካከታችው ከሥራ አፈናቅለው ፤ ከቀዬአቸው መንግለው ፤ በኤድስ ፤በርሃብ ፈጅተውብን አሳዳጊ አልባ አድርገውን ፤ ለጎዳና ተዳዳሪነት ዳርገውን መልሰው አደገኛ በዘኔዎች ብለው ሠየሙን እንጂ፤
- ለዩንቨርስቲ የበቁ ወንድም ፤ እህቶቻችንን ም ቢሆን በ1992 ፤ በ93፤ በ95 ፤ እና በ97 ኮሌጅ መኝታ ቤታቸው ድረስ በመሄድ በትግራይ ትግርኝ ጠባብ ተስፈንጣሪ አራጆች የወንድም እህቶቻችን ደም ፈሠሠ እንጂ ፤መቼስ ዘንግተን ነው፤
- በሕዝብ ደም የጠገቡ የዘመኑ ዘረኛ ሰካራሞች ባነሱት የዘር ጠብና አንባጓሮ የጥጋባቸው ማብረጃ፣ የዛራቸው መማለጃ ይሆን ዘንድ ባድሜ ላይ 100.000 ወጣቶችን በከንቱ አስፈጁት እንጂ፤
- አዋሣ ሎቄ መግቢያው ላይ የኮባ ቅጠል ይዘን ሰላማዊ ሠልፍ ስናደርግ 300 የምንሆን ወጣት ልጆች በወያኔ ተፈጀን እንጂ ፤
- ወጣት እህትቶቻችን የግፍ ሰለባ አድርገው ፤በገዛ ሀገራቸው መቆሚያ መሄጃ አሳጥተው የአረብ ሀገር ገርድ ለመሆን በወያኔ ኩባኒያ ከነነፍሳቸው ለከባድ ሥራና ለቱጃሮች ወሲብ ማርኪያ ተሸጡ እንጂ፤ መቼ የወያኔ ሥርዓት አሰበላቸው?

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com

- ከገብ ጀምሮ 19 ዓመት ይፈጁናል ፣ ያስፈጁናል ፣ያስርቡናል፣ ለዕፅ ይዳርጉናል ፣ሴቶችን ለሸርሙጥና ያመቻቹናል ፣ በዘር ያጫርሱናል፣ አንጂ መቼስ የኛ ሆነው ነው ? ዛሬ ላይ ቆመው መልሰው የኢትዮጵያን ወጣቶች ሊግ አያሉ ልጋጋቸውን የሚተፉብን ፤

በኛ እምነት ወያኔ ኢትዮጵያዊ ሆኖ የኢትዮጵያን ወጣቶች ሊያደራጀን ቀርቶ ሊያስብን መከጀሉ ይበልጥ ያስጠይፈናል እንጂ ልባችንን ከቶውንም አያገኛትም ።

- በፐ/ር አሥራት ቀብር ላይ ዘመርክ ተብሎ የተገደለው የሃያ አንድ ዓመቱ ወጣት አለምአንት አመንጋ የተገደለው በወያኔ፤
- ወጣት ስንታየሁ ታደሰ አባ ገ/ መድህን ተቃወምክ ተብሎ ልደታ ቤተክርስቲያን የተገደለው በወያኔ ፤
- ኤርትራ መለየት የለባትም ስላለ ወጣት ተስፋህን በሣንጃ የታረደው በወያኔ

- ወጣቱ ባህታዊ ፈቀደ ሥላሴ ተስፋዬ የተገደለው በወያኔ ፤
- አሰፋ ማሩንና ተስፋዬ ታደሰን ቀሰፎ ልጆቻቸውን ወላጅ አልባ ያደረገው ወያኔ ፤
- ጎንደር አደባባይ ኢየሱስ ወጣት መዘምራንን ጨጭፎ የረፈረፈው ወያኔ፤
- በአናዋር መስጊድ ወጣቶችን የፈጀው ወያኔ
- በ 97 ምርጫ የ21 ና የ17 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ የነበሩ ወጣት ሴቶቻችን ወጣት ሽብሬ ደሳለኝና ወጣት መሰርት ታደሰ ን ፤ የቀጨው ወያኔ ፤
- በምርጫ ተሸንፎ ሲያፍር ተቃውሟቸውን ያሰሙትን በመቶ የሚቆጠሩ ወጣቶችን የፈጀ ወያኔ፤ 30000 ወጣቶችን ደዴሳና ዙዋይ ላይ ለአዞና ለጊንጥ ያሰጣ ወያኔ፤
- አሁን እንኳን በቅርቡ ቱጃሩ አላሙዲና ወያኔ እያደርጉ ያሉትን ዘረፋ በመቃወማቸው የሻኪሶ ወጣቶችን ተኩስ ከፍቶ የገደለው ወያኔ

እንዴት ያለ የሞራል ብቃት ኖሮት ነው በሰላይ ልጆቹ አማካኝነት በዓለም ዙርያ የወጣቶች ሊግ አዋቅራለው የሚለን ?

ጎበዝ ተንቀናል ዘጠኝ ሞት መጣ ቢሉት አንዴ ግባ በለው እንዳለው ጀግና አንድ ነፍስ ይዘን ዘጠኝ ጊዜ ሞት ፤ መፍቀድ የለብንም ። ውርደትም ሞት ነው፤ ባርነትም የከፋ ሞት ነው፤ ተገዥነትም ሌላው አይነት ሞት ። ስለዚህ እኒህ ወያኔዎችና ዲቃላዎቻቸው እኛ ወጣቶችን ሊድፍሩ ሲከጅሉ አይገባም ነው መፍከራችን። መደራጀትና ተደራጅቶም መታገል ኢትዮጵያን ከዘመናዊ ባርነት ያድናታልና ፤ ኢወከንድ ኢትዮጵያዊ ነፍስ ያለው የወጣት ድርጅት ስለሆነ ፈልጉንና እንደባለቅ ፤ ለሀገር ስንል።

ኢትዮአሜሪካን አክሽን ሊግ ፤ የወጣቶች ሊግ ምንትስ እያለ ወያኔ ከሀገር እስከውጪ በኢትዮጵያ ዊ ሽማ ተደርቦ ሲመጣ ሽማውን ገፈን ዕርቃኑን እናስቀራለን እንጂ በሚሰምጠው የወያኔ መርከብ ተሳፋሪ እንዳማንሆን በቁርጠኝነት መግለጽና ማሳፈር አለበን ሲል ለኢትዮጵያ ወጣቶች ኢወከንድ መልዕክት ያስተላልፋል ።

ያለቀለት የወያኔ ሥርዓትን በወጣት ወያኔ ሊግ ለመጠገን የሚደረገውን ጉድ ጉድ በኢወከንድና በተቀሩ ሀገር ወዳደ ኢትዮጵያዊ ወጣቶች ክንድ ይገደባል ።

የኢትዮጵያን ወጣቶች ጠላት የሆነውን ወያኔን

በክንዳችን እናስወግዳለን።

ኢወከንድ ግ/5

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com